# ለ1997 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮግራም የተሻሻለው የበጀት ጥያቄ

ታህሣሥ 1995

አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ

**ተራ ቁጥር** | **ገ ጽ**


| ተራ ቁጥር | | ገ ጽ |
|---|---|---|
| 1.0 | መግቢያ ---------------------------------------- | 1 |
| 1.1 | የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራና የግብርና ቆጠራ ካርታዎች፣ ቁሳቁሶችና የአሠራር ስልቶች ለ1995 የቆጠራ ካርታ የሚሰጡት ድጋፍ ---------------- | 2 |
| 1.2 | ለቆጠራ ካርታ ሥራ የተለያዩ የፌዴራል መ/ቤቶች እገዛ---------------------------------------- | 4 |
| 1.3 | በክልሎች ሊደረጉ የሚችሉ እገዛዎች ------------- | 5 |
| 1.4 | ለቆጠራ ካርታ ሥራ ማካሄጃ የቀረበ የወጪ ዝርዝር - | 5 |
| 2.0 | የተስተካከለው በጀት --------------------------- | 7 |
| 2.1 | አማራጭ አንድ ---------------------------------- | 7 |
| 2.2 | አማራጭ ሁለት ---------------------------------- | 8 |
| 3.0 | ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ------------------------ | 8 |
| 4.0 | አባሪዎች ---------------------------------------- | 11 |

# ለ1997 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮግራም የተሻሻለ የበጀት ጥያቄ

## 1. መ ግ ቢ ያ

የሚኒስትሮች ም/ቤት ኀዳር 20 ቀን 1995 ዓ.ም ባካሄደው 55ኛ መደበኛ ስብሰባ በ1997 ዓ.ም ለሚካሄደው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ በቀረበው የበጀት ጥያቄ ላይ ከተወያየ በኋላ፦

1. የ1987 ዓ.ም የሕዝብና ቤት ቆጠራና አጠቃላይ የግብርና ቆጠራ ሲካሄድ የተጠቀምንባቸው ካርታዎች፣ ቁሳቁሶችና የአሠራር ስልቶች ለ1997 አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ምን ያህል ድጋፍ እንደሚሰጡ፣

2. ለፕሮግራሙ የተለያዩ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ለምሳሌ የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ባለሥልጣንን፣ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን፣ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣንን፣ ...ወዘተ እገዛ በመጠቀም ምን ያህል የፕሮግራሙን ክፍል ለመሸፈን እንደሚቻል፣

3. በክልሎች ሊሸፈን የሚችለውን የሥራ ድርሻ በመለየት (አዳራሽ፣ አስተርጓሚ፣ ...ወዘተ)

4. ፕሮግራሙን ለማካሄድ የተሰላው ወጪ በዝርዝር እንደገና ከተሠራ በኋላ ወጪዎቹ በትክክል አስፈላጊ መሆን አለመሆናቸውን በመፈተሽ፣

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አስተባባሪነት፦

- የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
- የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት፣
- የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን፣
- የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ባለሥልጣን እና
- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

አባል የሆኑበት ኮሚቴ ተቋቁሞ የበጀት ጥያቄው እንደገና ታይቶ እንዲቀርብ መመሪያ ሰጥቷል።

ከሚኒስትሮች ም/ቤት የተሰጠውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ኮሚቴው ከላይ የተጠቀሱትን 4 ነጥቦች ባደረጋቸው ስብሰባዎች አንድ በአንድ ተመልክቶታል።

1.1 <u>የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራና ግብርና ቆጠራ ካርታዎች፣ ቁሳቁሶችና የአሠራር ስልቶች ለ1995 የቆጠራ ካርታ የሚሰጡት ድጋፍ:-</u>

የ1987 የቆጠራ ካርታን በማደስ/ወቅታዊ በማድረግ ወጪ መቀነስ መቻል አለመቻሉ፣ አለበለዚያም አዲስ የቆጠራ ካርታ መሥራት አስፈላጊ ስለመሆኑ ኮሚቴው በሰፊው ተወያይቷል። በውይይቱ ወቅት ለውሳኔ እንዲረዳ የቆጠራ ካርታ እንደአዲስ መሥራት ስለአስፈለገበት ምክንያትና ስለቆጠራ ካርታ ሥራ ዓላማ ገለጻ ቀርቦ ከታየ በኋላ ኮሚቴው በሙሉ ድምፅ የቆጠራ ካርታ እንደአዲስ መሠራት እንዳለበት ተስማምቷል። ይሁን እንጂ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቆጠራ ካርታ ሥራ ሳያስፈልግ ካሳለፈው የምርጫ ተሞክሮው በቀላል ወጪ ቆጠራ እንዴት እንደሚካሄድ የሚገልጽ የአሠራር ስልት አቅርቦ ኮሚቴው በዚህም ላይ በስፋት ተወያይቷል።

በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቀረበው ሰነድ አጠቃላይ ይዘት :-

- ቆጠራው በየምርጫ ጣቢያ ላይ መዝጋቢዎች በመመደብ እያንዳንዱ ሰው እየመጣ ታዛቢዎች ፊት መረጃ እንዲሰጥ ማድረግና
- ውጤቱም በየቦታው ተለጥፎ ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን የሚጠቁም ነው።

በዚህ አዲስ በቀረበው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ስልት ላይ በተደረገው ውይይት:-

1. በቆጠራ የሚገኙ የግለሰብ መረጃዎች በምስጢር መያዝ እንዳለባቸውና በአደባባይ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ቆጠራ ሊካሄድ እንደማይችል፣

2. እያንዳንዱ ዜጋ በቆጠራ ወቅት ትክክለኛ መረጃ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት፣ ፈቃደኛ ካልሆነ የሚቀጣበት ሁኔታ በሕግ የተደነገገ መሆኑን፣

3. ለሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ስፋትና ጥልቀት ያላቸውና በምርጫ ወቅት ከሚፈለጉ መረጃዎች የተለዩ መሆናቸው፣

4. የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ከቤት ቤት በመሄድ የሚሰበሰብ መሆኑ፣

5. በኮሚሽኑ የቀረበው ቆጠራ ሕዝብን ብቻ የሚመለከት መረጃ ሳይሆን ቤቶችንም የሚመለከቱ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት በመሆኑ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቀረበው የአሠራር ስልት ቤተሰቦችና ቤቶች ሳይቆጠሩ እንዳይዘለሉና ከአንድ ጊዜ በላይ እንዳይቆጠሩ የማይረዳ ስልት በመሆኑ የቆጠራ ካርታ ሥራን የሚያስቀርና አጠቃላይ ቆጠራን የሚተካ አማራጭ አለመሆኑን ከቦርዱ በስተቀር በሁሉም የኮሚቴው አባላት ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በተሰካ ሁኔታ የመረጃው ጥራት ሳይጓደፍ፣ ቤተሰቦችና ቤቶች ሳይዘለሉና በድጋሚ ሳይቆጠሩ ለመቁጠር እንዲቻል የካርታ ሥራ ጠቃሚ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የ1987 የቆጠራ ካርታ መጠቀም ከወጪ አንፃርም ሆነ ሌሎች ካርታው ከሚሰጣቸው ጥቅሞች አንፃር ሲታይ አዲስ መሥራቱ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ ታምኖበታል፡፡ የቆጠራ ካርታ ሥራ እንደ አዲስ መሥራት ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የቆጠራ ካርታ ሥራ እንደ አዲስ ማከናወን ያስፈለገበት ምክንያት፡-

- የቀበሌ፣ የወረዳ፣ የዞንና የክልል ወሰኖች ለውጥ በመኖሩ፣
- ከ10 ዓመት በኋላ በየቆጠራ ቦታው የሕዝብ ብዛት ለውጥ በመኖሩ፣
- በ1987 በሥራ ላይ ያልዋለ አዲስ መሣሪያ (GPS) ለመጀመሪያ ጊዜ በመጠቀም ቆጠራውን ለማካሄድ የታሰበ መሆኑ፣
- ለማንኛውም ተከታታይ ጥናቶች (Surveys) አዲስ ፍሬም (Frame) አስፈላጊ መሆኑ፣
- ያለፈውን ካርታ ለማደስ ካርታ ሠራተኛ በየቆጠራ ቦታው የግድ መዞር ያለበት በመሆኑ፣
- የቆጠራ ካርታ ካልተሠራ የቆጣሪ ብዛት፣ የመጠይቅና ሌላም ለቆጠራው ተፈላጊ ሎጂስቲክስ ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት አስቸጋሪ በመሆኑ፣
- ከ10 ዓመት በፊት የነበሩት የቆጠራ ካርታ የወሰን ምልክቶች አሁን ሁሉም ላይኖሩ ስለሚችሉ ለውጡን በካርታ ውስጥ ማካተት አስፈላጊ መሆኑ፣

- ያለፈውን ካርታ እንጠቀም ቢባል እንኳ የቆጠራ ካርታዎች ፎቶ ኮፒ በማስፈለጉና ለዚህም ብዙ ውጪ የሚጠይቅ መሆኑ፣

- ቆጠራው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲኖረው በተለመደው አሠራር (በካርታ በተደገፈ) መከናወን ስላለበት::

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን /ማ.ስ.ባ/ በ1994 ባካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ ወቅት በ1985 የተዘጋጀውን ካርታ አድሶ መጠቀም ግድ ሆኖበት ስለነበረ ለዚህ በሚሊዮን ብር የሚቆጠር ወጪ ለማውጣት ተገዶ ነበር:: ከዚህ መገንዘብ የተቻለው እንደገና መሥራቱ አስፈላጊ መሆኑን ነው:: ቁሳቁሶችን በተመለከተ ላለፈው ቆጠራ ተገዝተው የነበሩ ቁሳቁሶች አብዛኞዎቹ አርጅተው ለአገልግሎት የማይበቁና የተቀሩት ደግሞ በጨረታ የተሸጡ መሆኑን ከማ.ስ.ባ ተገልጿል::

## 1.2 ለቆጠራ ካርታ ሥራ የተለያዩ የፌዴራል መ/ቤቶች እገዛ:-

ኮሚቴው በተሰጠው መመሪያ መሠረት የኮሚቴው አባላትና ሌሎች መ/ቤቶችን እገዛ በመጠቀም ምን ያህል ወጪን መቀነስ እንደሚቻል በስፋትና በጥልቀት ተወያይቶ በተጨባጭ የተገኙ ምላሾችንና ይገኛሉ ተብሎ ታሳቢ የተደረጉትን መሠረት በማድረግ ወጪዎች እንዲቀነሱ አድርጓል:: በዚህ መሠረት፣

ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን:-

- 100 ድንኳኖችና ከ50 በላይ ተሽከርካሪዎች እንደሚገኙ ተገምቷል:: በዚሁ መሠረት ለድንኳን ተይዞ ከነበረው በጀት የ100 ድንኳኖች ዋጋ ተቀንሷል::
- ከመጋቢት ወር 1995 በኋላ በአሠልጣኝነትና በአስተባባሪነት የሚያገለግሉ ሠራተኞችን ማግኘት እንደሚቻል ታውቋል::
- ለነዚህ ሠራተኞች ደመወዝ በባለሥልጣኑ መ/ቤት በኩል እንደሚሸፈን ስለታሰበ በጀት አልተያዘም::

የካርታ ሥራ ባለሥልጣን:-

ለቆጠራ ካርታ ሥራ መነሻ የሚሆን Topographic Maps በጣም አስፈላጊ ነው:: ቀደም ባሉት ጊዜያት እነዚህ ካርታዎች ከካርታ ሥራ ባለሥልጣን የሚገዙ በመሆናቸው ብር 158,688 ለካርታ ግዥ ተይዞ ነበር:: ነገር ግን የካርታ ሥራ ባለሥልጣን እነዚህን ካርታዎች በነፃ እንደሚሰጥ በመግለጹ የተያዘው በጀት እንዲቀነስ ተደርጓል::

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ:-

ለቆጠራ ካርታ ሥራ የሚያገለግሉ የመስክ ዕቃዎች፣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ዕቃዎች ካላቸው እንዲሰጡ ተጠይቀው የመስክ ዕቃዎችና ተሽከርካሪዎች እንደሌሉአቸው በመግለጽ በሕትመት ሥራ ብቻ ሊተባበሩ እንደሚችሉ ገልጸዋል።

የሕትመት ሥራን በተመለከተ ቀደም ሲል የተያዘው በጀት ለወረቀትና ለሕትመት ቀለሞች መግዣ ብቻ ስለነበር በጀቱ ሲቀርብ የሕትመት ሥራዎቹ በሙሉ በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ይሠራሉ ተብሎ የታሰበ ቢሆንም የ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤት ገና ያልታተመ በመሆኑ ከፍተኛ ሥራ የሚሠራ ስለሆነ ሙሉ በሙሉ የቆጠራ ካርታ ሥራ ዶኩመንቶችን ማተም እንደሚቸገር ባለሥልጣኑ ግልጿል። ስለዚህ የቆጠራ ካርታ ሥራ ዶኩመንቶች ሕትመት በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ትብብር እንደሚሰራ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

## 1.3 በክልሎች ሊደረጉ የሚችሉ እገዛዎች:-

ክልሎች የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አባል በመሆናቸውና በውጤቱም ተጠቃሚ መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት የክልሎች እገዛ ምን መሆን እንዳለበት ኮሚቴው ውይይት አካሂዷል።

በዚሁ መሠረት በ1995 የበጀት ዓመት:-

- ሥልጠና አዳራሾች በክልሎች ትብብር በነፃ ይገኛል ተብሎ በማሰብ ለዚህ ተይዞ የነበረው በጀት ተቀንሶ ለጥቃቅን ወጪዎች ብቻ ማለትም ለውሃ፣ ለመብራት ለጽዳት፣ ...ወዘተ አነስተኛ በጀት ተይዟል።
- ከረዳት ካርታ ሠራተኞችና ከተቆጣጣሪዎች ጋር የወረዳዎችንና የቀበሌዎችን ወሰን አብረው በመዞር የሚያሳዩ መንገድ መሪዎች፣ አስተርጓሚዎችና አስተባባሪዎች ከክልሎች በትብብር እንደሚገኙ በማሰብ ለዚህ ተይዞ የነበረው በጀት እንዲቀር ተደርጓል።

## 1.4 ለቆጠራ ካርታ ሥራ ማካሄጃ የቀረቡ የወጪ ዝርዝር:-

ካለፉት ሁለት የቆጠራ ካርታ ሥራዎች በመነሳት ያስፈልጋሉ የተባሉት የመስክ ዕቃዎችና በሥራው ላይ ለሚሠማሩ ሠራተኞች የሚያስፈልገው የደመወዝ፣ የውሎ አበልና የሥራ ማስኬጃ በጀት በኮሚቴው በዝርዝር ከታየ በኋላ የሚከተሉት ማሻሻያዎች ተደርጓል።

የምግብ ማብሰያ ቁሳቁሶች:-

የቆጠራ ካርታ ሥራ ቡድኖች በካምፕ እየኖሩ በመስክ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ በመሥራት መረጃ ከሰበሰቡ በኋላ በካምፕ በመሆን ካርታ ያዘጋጃሉ:: ስለዚህ በየገጠሩ ምግብ በግዥ መልክ ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ ለምግብ ፍለጋ የሚጠፋውን ጊዜ ለማስቀረት የምግብ ማብሰያ ቁሳቁሶች በመንግሥት እንደሚቀርብ ታስቦ በጀት ቀርቦ ነበር:: አሁን ተሻሽሎ በቀረበው በጀት መሠረት የምግብ ማብሰያ ቁሳቁሶች ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣንና ከሌሎች መ/ቤቶች በትብብር እንደሚገኙ በማሰብ ለዚህ ተይዞ የነበረው በጀት ተሰርዟል::

ደመወዝ:-

ቀደም ሲል በቀረበው የበጀት ዝርዝር ላይ እንደተመለከተው የመስክ ሠራተኞች ከሥልጠናው ቀን ጀምሮ ተቀጣሪ እንደሆኑ ታስቦ ነበር:: ነገር ግን አሁን በቀረቡት አማራጮች የተቆጣጣሪዎችና ረዳት ካርታ ሠራተኞች ቅጥር ከሥልጠና በኋላ እንደሚጀምር በማሰብ ለሁለት ወር ተይዞ የነበረው በጀት ተቀንሷል::

አ በ ል:-

- የመስክ ዕቃዎች ድንኳኝ፣ አልጋና የመኝታ ከረጢት በማሟላት ከቀን የአበል ወጪ ላይ 40% የአልጋ በመቀነስ አበል መክፈል ይቻላል በማለት ማሻሻያ ተደርጓል::

- ከግብርና ናሙና ቆጠራ ተሞክሮ በሥልጠና ወቅት ሙሉ አበል ሳይከፈል ለተቆጣጣሪዎች በቀን ብር 30፣ ለረዳት ካርታ ሠራተኞችና ለሹፌሮች ብር 25 ይከፈላል በማለት ከፍተኛ የበጀት ቅነሳ ተደርጓል::

በሁለተኛው የቆጠራ ካርታ ሥራ ወቅት ለመስክ ሠራተኞች ሙሉ አበል እየተከፈለ፣ የካምፕ ዕቃዎች ማለትም ድንኳኝ፣ አልጋና የመኝታ ከረጢት እንዲሁም የምግብ ማብሰያ ቁሳቁሶች ተሟልቶ ቀርቦ ነበር::

የሥራ ማስኬጃ:-

በተመሳሳይ ሁኔታ ለሥራ ማስኬጃ ተይዞ የነበረውን የበጀት ዝርዝር አንድ በአንድ ታይቶ የተወሰኑ ውጪዎች ተቀንሷል:: ቅናሹ የተደረገው የሚከተሉትን ማለትም፣

- ለቆጠራ ካርታ ሥራ ከየመ/ቤቱ በትብብር የሚገኙ መኪናዎች አጭር ጊዜ ያገለገሉና የጥገና ወጪያቸው ብዙ እንደማይሆን በማሰብ ለጥገና ለእያንዳንዱ መኪና ተይዞ ከነበረው በጀት በማስተካከል/በመቀነስ፣

- በትብብር የሚገኙ መኪናዎች በሙሉ የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል በማለት ለመድን ተይዞ የነበረውን በጀት ሙሉ በሙሉ በመሰረዝ፣

- በተጨማሪ መኪናዎቹን የሚሰጡ መ/ቤቶች/ድርጅቶች ለ6 ወራት የሚያገለግሉ ጎማዎች በመግጠም እንዲሰጡ ታሳቢ በማድረግ ለጎማ ተይዞ የነበረውን በጀት ከግማሽ በላይ በመቀነሱ ነው።

## 2.0 የተስተካከለው በጀት

ከላይ የተገለጹትን መሠረት በማድረግ በጀቱ በሁለት አማራጮች የቀረበ ሲሆን የእነዚህ አማራጮች ጥቅምና የሚያስከትሉት ችግር ለውሳኔ እንዲረዳ ቀጥሎ ቀርቧል።

## 2.1 አማራጭ አንድ

በአማራጭ አንድ የቀረበው የቆጠራ ካርታ ሥልጠና ከጥር - መጋቢት 1995 እና ዋናው የመስክ ሥራ ከሚያዝያ - ሰኔ 1995 ዓ.ም. እንደሚሆን ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን በዚህ አማራጭ መሠረት ተደግፎ የቀረበው በጀት ብር 11,837,061 ነው።

### የሚኖረው ጥቅም

1. ቀደም ሲል የቀረበው የቆጠራ ካርታ ሥራ ይጠናቀቃል ተብሎ የተገመተው በ130 ቡድን በ28 ወራት ውስጥ ነው። እስከአሁን ከታሰበው ጊዜ በ5 ወር የዘገየ በመሆኑ ከዋናው ቆጠራ በፊት ለማጠናቀቅ በአፋጣኝ የካርታ ሥራ መጀመሩ በርካታ የካርታ ሥራ ቡድኖች ከመጨመር ያድናል። ከዚሁ ጋር የተያያዙ የመስክ ዕቃዎችም ስለማይጨምሩ ወጪው ይቀንሳል።

2. የኮሚሽኑ መ/ቤት ያለው ሠራተኛ ውሱን በመሆኑ በአነስተኛ የካርታ ሥራ ቡድን መጀመር ሥራውን በደንብ ተቆጣጥሮ ለማሠራት ያስችለዋል፣

3. በ1995 ሥራው ቢጀመር በ1996 ሊኖር የሚችለውን የበጀት ጫና ይቀንሳል፣

4. የካርታ ሥራው በ1995 የሚጀመር ከሆነ ለሥራው ከሌሎች መ/ቤቶች፣ ክልሎች፣ ...ወዘተ የሚጠየቁት ሠራተኞች፣ ተሽከርካሪዎች ... ወዘተ ቁጥር አነስተኛ ይሆናል።

የሚያስከትለው ችግር:-

አሁን ካለው የፋይናንስ ችግር አንፃር ሲታይ የሚያስፈልገውን በጀት ለመመደብ አስቸጋሪ ይሆናል።

## 2.2 አማራጭ ሁለት

በአማራጭ ሁለት የቆጠራ ካርታ ሥራ የአሰልጣኞች ሥልጠና በሰኔ ወር 1995 እንደሚካሄድና የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና የካርታ ሥራው በ1996 እንደሚጀምር ታሳቢ በማድረግ ተደግፎ የቀረበው በጀት ለአሠልጣኞች ሥልጠና ብር 956,852 ነው።

የሚኖረው ጥቅም:-

በበጀት ዓመቱ የሚደረገው እንቅስቃሴ አነስተኛ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት አገሪቷን ከገጠማት የፋይናንስ ችግር አንፃር ሲታይ በበጀት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ አነስተኛ ይሆናል።

የሚያስከትለው ችግር:-

በ1995 ሊሠራ የታሰበው የካርታ ሥራ ወደ 1996 በመሸጋገሩ ፣

- ለካርታ ሥራው የሚያስፈልገው ቡድን ከ130 ይጨምራል፣
- ከዚህ ጋር ተያይዞ አስፈላጊው የተሽከርካሪ፣ የመስክ ቁሳቁስ፣ የሠልጣኞች፣ የተቆጣጣሪዎች፣ የGPS መሣሪያዎች ቁጥር ስለሚጨምር የበጀት ጫናውም ከፍተኛ ይሆናል።

## 3.0 ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች:-

የቆጠራ ካርታ ሥራ አገር አቀፋዊ ይዘት ያለው በመሆኑ በርካታ ቁጥር ያለው የሰው ኃይል፣ ከፍተኛ ገንዘብና ሰፊ ጊዜ የሚጠይቅ ተግባር ነው። ይህን ግዙፍ ሥራ አንድ መ/ቤት ብቻውን የሚወጣው ተግባር አይደለም። ስለሆነም የካርታ ሥራ በጀቱ የሌሎች የፌዴራል መ/ቤቶችንና የክልል መንግሥታትን ድጋፍ ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

በዚሁ መሠረት የሌሎችን ትብብርና እገዛ ታሳቢ በማድረግ በሁለቱ አማራጮች የበጀት ቅነሳ ተደርጓል።

ይሁን እንጂ ታሳቢዎቹ ካልተሟሉ አሁን የቀረበው በጀት ከፍተኛ ጭማሪ ያስከትላል። በመሆኑም በጀቱ ሲፈቀድ ታሳቢ የተደረጉት ሁሉ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚሟሉበት ሁኔታ በግልጽ መመሪያ ሊሰጥበት ይገባል። በተለይ፣

1. ብዛታቸው 50 የሆነው የካርታ ሥራ አስተባባሪዎች ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በትብብር እንደሚገኙና ደመወዛቸውንም የባለሥልጣኑ መ/ቤት እንደሚከፍላቸው በማሰብ የደመወዝ በጀት አለመያዙ፣

2. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሌሉትና ሥራውም በየገጠሩና በከተማው ቀበሌዎች የሚካሄድ በመሆኑ ክፍያዎችን ለመፈጸም አያመችም። በዚሁ ምክንያት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በመጠቀም ለመስክ ሠራተኞች ክፍያ እንደሚፈጸም ታስቧል። ዝርዝሩ ወደፊት ውይይት የሚደረግበት ሆኖ የሂሳብ ሠራተኞች፣ ገንዘብ ያዥና ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ይገኛሉ በማለት ለእነዚህ ሠራተኞች የደመወዝ በጀት አልተያዘም።

3. ሠራተኞች በካምፕ እንዲኖሩ ማድረጉ ለሥራው ቅልጥፍናና ጥራት ወሳኝ በመሆኑ ካምፑ እንደ ጽ/ቤትም ሆኖ ስለሚያገለግል ጥቅሙ ለሠራተኞች ብቻ ሳይሆን ለኮሚሽኑ ጽ/ቤትም ጭምር በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። ለተገለጸው ዓላማና ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን የበጀት ቅናሽ (40% የአልጋ) ለማድረግ እንዲረዳ የካምፕና የመስክ ሥራ መገልገያ ቁሳቁሶች በትብብር ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣንና ከሌሎች መ/ቤቶች በትብብር እንደሚገኙ ታስቧል። ይህ ካልሆነ ሙሉ አበል የሚከፈል በመሆኑ ሥራው በሚታሰበው ጥራትና ፍጥነት ሊሠራ አይችልም።

4. በቆጠራ ካርታ ሥራ ላይ የሚሠማራው የሰው ኃይል ከፍተኛ በመሆኑ፣ የመስክ ቁሳቁሶችን በመጫን ከቦታ ቦታ መዘዋወር የግድ በመሆኑና ሠራተኞች ከሠፈሩበት ካምፕ እየራቁ ሲሄዱ በመኪና መሸኘት/ማድረስና ካምፕ ሲቀይሩ መኪና መኖር ለሥራው መቀላጠፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ስለሆነም ለእያንዳንዱ ቡድን መኪና አስፈላጊ ነው። የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ምንም ዓይነት የመስክ ተሽከርካሪ የሌለው ስለሆነ ለሥራው የሚያስፈልጉት ሁሉ በትብብር ከሌላ ቦታ እንዲሟሉለት በታሳቢ የተደረገ ሲሆን የተባለውን መጠን ተሽከርካሪ ማሰባሰብ ቀላል አለመሆኑ ታውቆ ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው።

5. ለጥገና የተያዘ ወጪ አነስተኛ በመሆኑ፣ ለመድን ዋስትና ምንም ዓይነት በጀት ያልተያዘና ለጐማ ከመጠባበቂያ በስተቀር የተያዘ በጀት አለመኖሩ ታውቆ በትብብር የሚመጡ መኪናዎች ብዙ ያላገለገሉ፣ የመድን ሽፋን ያላቸውና የተገጠመላቸው ጐማ ቢያንስ ለ6 ወራት ሊያገለግል የሚችል መሆን እንዳለበት መመሪያ እንዲሰጥበት።

# 4.0 አባሪዎች

## የ1997 የሕዘበና ቤት ቆጠራ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ በጀት

ማጠቃስያ

| ተ.ቁ | ዋና ዋና የበጀት ርዕሶች | በፊት የቀረበ | | ተሻሽሎ የቀረበ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማራጭ አንድ 1995 | አማራጭ ሁለት 1995 | አማራጭ አንድ በ1995 ከተሰራ | አማራጭ ሁለት 1995 |
| 1 | ደመወዝ | 4,665,560 | 4,365,560 | 1,217,190 | |
| 2 | አበል (በመስክ ስራ ወቅት) | 15,173,252 | 15,173,252 | 3,181,062 | |
| 3 | ስልጠና | 4,843,440 | 4,502,440 | 2,490,570 | 268,810 |
| 4 | የመስክ ዕቃዎች | | | | |
| | ሀ. ቋሚ ዕቃዎች | 3,084,234 | 3,084,234 | 1,945,930 | |
| | ለ. አላቂ ዕቃዎች | 1,457,905 | 1,457,905 | 433,947 | |
| 5 | ስራ ማስኬጃ | | | | |
| | (ነዳጅ፣ ጥገና፣ ኢንሹራንስ . . . ወዘተ) | 10,746,200 | 10,746,200 | 2,003,625 | |
| 6 | ሕትመት | 564,737 | 564,737 | 564,737 | 688,042 |
| 7 | ለተሽከርካሪዎች ግዢ | 48,198,000 | | | |
| | ድምር | 88,733,328 | 39,894,328 | 11,837,061 | 956,852 |

# አማራጭ - 1 (1995)

የ 1997 አገር አቀፍ ሕዝብና ቤት ቆጠራ የካርታ ስራ በጀት

| የቆጠራ ዝግጅት | 1995 EFY | መጠን | ዋጋ | 1995 |
|---|---|---|---|---|
| የካርታ ስራ መመሪያናየካርታ ስራ ቅደም ተከተል የመስክ ሙከራ | 5,000 | | | |
| የመመሪያዎችና ቅፆች ህትመት (ዝርዝሩ ከዚሕ ጋር አባሪ ሆኗል) | 564,737 | | | |
| ለካርታ ሥራ ቀሰቀሶች ጥገና (ፕሪንተር፣ ፕሎተር የፎቶ ኮፒ ማሽን... ወዘተ) በዋናው መ/ቤት | 6,000 | | 2,000 ብር/በወር | 3 ወራት |
| ለስልክና ሌሎች መገናኛዎች በቅ/ጽ/ቤትና ቡድን | 78,000 | 130 ቡድን | 200 ብር/በቡድን | 3 ወራት |
| ለስልክ ኢሜልና ሌሎች መገናኛ በዋናው መ/ቤት | 15,000 | | 5,000 ብር/በወር | 3 ወራት |
| አላቂ ቁሣቁሶች | 19,500 | 130 ቡድን | 50 ብር/በቡድን | 3 ወራት |
| ለመስክ ቁሳቁስ ጥገና (ድንኳን፣ አልጋ ...ወዘተ.) | 39,000 | 130 ቡድን | 100 ብር/በቡድን | 3 ወራት |
| የሌሎች (ንዑስ ድምር) | 2,568,362 | | | |
| ድምር (መጠባበቂያን ሳይጨምር) | *11,837,061* | | | |
| | | | | |
| መጠባበቂያ 20 ፐርሰንት | 0 | | | |
| | | | | |
| ጠቅላላ ድምር | *11,837,061* | | | |

# አባሪ ለአማራጭ - 1 (1995)

የመስክ ስራ በ 28 ወራት ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት 130

| በ1995 ዓ.ም መዝሐት ያለባቸው አላቂ ቁሳቁሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተራ ቁጥር | ቁሳቁሶች | ጠቅላላ ብዛት | ያንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ |
| 1 | አዛሊድ ወረቀት (በጥቅል) | 300 | 0 | 0.00 |
| 2 | አሞኒያ ኬሚካል (ሊትር) | 1,000 | 0 | 0.00 |
| 3 | የስእል ቀለም (1.4) ሊትር | 100 | 162.00 | 16,200.00 |
| 4 | ላፒስ (የእርሳስና የቀለም) | 8,218 | 1.10 | 9,039.80 |
| 5 | እርሳስ (Sh.H.HB) | 15,000 | 0.50 | 7,500.00 |
| 6 | ማስኪንግ ቴፕ | 6,798 | 6.45 | 43,847.10 |
| 7 | መሜ | 1,749 | 4.80 | 8,395.20 |
| 8 | መቅረጫ (አነስተኛ) | 2,002 | 2.50 | 5,005.00 |
| 9 | ጠረጴዛ ላይ የሚታሰር መቅረጫ | 136 | 58.00 | 7,888.00 |
| 10 | እስክሪቢቶ (ጥቁር) | 5,000 | 1.03 | 5,150.00 |
| 11 | ማስታወሻ ደብተር ( 100 ገጽ) | 3,000 | 6.50 | 19,500.00 |
| 12 | ማርከር (መካከለኛ) ቀይ | 1,100 | 5.50 | 6,050.00 |
| 13 | ማርከር (መካከለኛ) የተለየ ቀለም | 1,100 | 5.50 | 6,050.00 |
| 14 | ሲሎ ቴፕ | 8,651 | 3.40 | 29,413.40 |
| 15 | ክላሰር | 20,000 | 0.80 | 16,000.00 |
| 16 | የስቴፕለር ሽቦ (ፓኬት) | 1,430 | 2.75 | 3,932.50 |
| **17** | **መነሻ ካርታ 1:50000** | **13,224** | **0.00** | **0.00** |
| 18 | የፎቶ ኮፒ ወረቀት A3 (ፓኬት) | 440 | 129.00 | 56,760.00 |
| 19 | የፎቶ ኮፒ ወረቀት A4 (ፓኬት) | 110 | 43.40 | 4,774.00 |
| 20 | ሄቪ ዲዩቲ ባትሪ ድንጋይ በሳምንት 4 ለየቡድኑ ለ30 ወራት | 22,000 | 5.00 | 110,000.00 |
| 21 | የራዘር ምላጭ (ፓኬት) | 6,006 | 2.50 | 15,015.00 |
| 22 | ቾክ | 1,464 | 6.50 | 9,516.00 |
| 23 | ባትሪ | 143 | 12.00 | 1,716.00 |
| 24 | የባትሪ ድንጋይ | 8,580 | 4.00 | 34,320.00 |
| 25 | ተጣጣፊ ጠረጴዛ | 143 | 125.00 | 17,875.00 |
| 26 | ጀንጥላ | 1,144 | 0.00 | 0.00 |
| | ጠቅላላ ድምር | | | **433,947.00** |

# አማራጭ - 2 (1995)

## የቆጠራ ካርታ ሥራ የአሰልጣኞች ስልጠና የ1995 በጀት

| የቆጠራ ዝግጅት | 1995 EFY | መጠን | ዋጋ | 1995 |
|---|---|---|---|---|
| 1. ስልጠና | | | | |
| ስልጠና በዋናው መ/ቤት | | | | |
| የጽሕፈት መሣሪያ | 2,560 | 20 ብር/በሰልጣኝ | 128 ሰልጣኞች | |
| ትራንስፖርት- ለካርታ ሥራ አስተባባሪዎች መሄጃና መመለሻ | 24,000 | 400 ብር/በሰልጣኝ | 60 ሰልጣኞች ከማ.ስ.ባ ቅ/ጽ/ቤት | |
| ትራንስፖርት- ለዋናው መ/ቤት ሰልጣኞች | 10,800 | 6 ብር/በሰልጣኝ | 60 ሰልጣኞች ከሕ.ቤ.ቆ.ኮ ጽ/ቤት እና ማ.ስ.ባ ዋና መ/ቤት | 30 ቀናት |
| ትራንስፖርት- ለመስክ ሙከራ | 9,600 | 20 ብር/በሰልጣኝ | 120 ሰልጣኞች | 4 ቀናት |
| የምሣ አበል- ለዋናው መ/ቤት ሰልጣኞች | 36,720 | 18 ብር/በሰልጣኝ | 68 ሰልጣኞች ከዋ/መ/ቤት | 30 ቀናት |
| ነዳጅ- ለአራት መኪኖች | 7,200 | 60 ብር/በመኪና | 4 መኪና | 30 ቀናት |
| የአዳራሽ ኪራይ- ለዋናው መ/ቤት ስልጠና | 0 | 0 | | 0 |
| ለአንድ ወር ለእረፍት ጊዜ ሻይ የሚወጣ | 7,680 | 60 ብር/በሰልጣኝ | 128 ሰልጣኞች | |
| ሥልጠና- ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች | 17,500 | 25 ሰው | 70 ብር/በቀን | 10 ቀናት |
| ሾፌሮች- የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችን የሚያመጡ | 11,750 | 25 ሰው | 47 ብር/በቀን | 10 ቀናት |
| ነዳጅ ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች መኪና- ለሥልጠና ሲመጡ | 15,000 | 600 ብር/በመኪና | 25 ቅ/ጽ/ቤት | |
| አበል- ለካርታ ሥራ አስተባባሪዎች ዋናው መ/ቤት ሲሰለጥኑ | 126,000 | 60 ሰው | 70 ብር/በቀን | 30 ቀናት |
| የሥልጠና ንዑስ ድምር | 268,810 | | | |
| 2. ለስልጠናና ለዋናው ሥራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ መመሪያዎችና ቅጾች ህትመት | 688,042 | | | |
| ጠቅላላ ድምር | 956,852 | | | |

# አማራጭ - 2 (1996)

የቆጠራ ካርታ ስራ የ1996 በጀት ፍላጎት 202 ቡድን

| የቆጠራ ዝግጅት | 1996 EFY | መጠን | ዋጋ | 1996 |
|---|---|---|---|---|
| 1 የሰው ሐይል | | | | |
| ሀ.ደሞዝ | | | | |
| ተቆጣጣሪ | 1,535,200 | 202 ሰው | 760 ብር/በወር | 10 ወራት |
| ረዳት ካርታ ስራተኞች | 4,617,720 | 1212 ሰው | 381 ብር/በወር | 10 ወራት |
| የህትመት ሠራተኞች | 19,080 | 3 | 530 ብር/በወር | 12 ወራት |
| የንብረት ክፍል ሠራተኞች | 10,600 | 2 | 530 ብር/በወር | 10 ወራት |
| የካርታ ሥራ አስተባባሪዎች | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ሂሣብ ሠራተኞች | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ገንዘብ ያዦች | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ተላላኪዎች | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ጽዳት ሠራተኞች | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ሾፌሮች | 117,000 | 30 ሰው | 325 ብር/በወር | 12 ወራት |
| የካምፕ ዘበኞች | 0 | 0 | 0 | 0 |
| የደሞዝ (ንዑስ ድምር) | *6,299,600* | | | |
| ለ. አበል | | | | |
| ካርቶግራፈር | 14,000 | 2 ሰው | 70 ብር/በቀን | 100 ቀናት |
| ኮምፓይለሮች | 70,000 | 10 ሰው | 70 ብር/በቀን | 100 ቀናት |
| የካርታ ሥራ አስተባባሪዎች | 696,000 | 60 ሰው | 58 ብር/በቀን | 200 ቀናት |
| ተቆጣጣሪዎች | 2,108,880 | 202 ሰው | 34.8 ብር/በቀን | 300 ቀናት |
| ረዳት ካርታ ስራተኞች | 10,253,520 | 1212 ሰው | 28.2 ብር/በቀን | 300 ቀናት |
| ሾፌሮች | 1,903,500 | 225 ሰው | 28.2 ብር/በቀን | 300 ቀናት |
| የካምፕ ዘበኞች | 424,200 | 202 ቡድን | 7 ብር/በቀን | 300 ቀናት |
| መንገድ መሪዎች/ድንበሮችን የሚያሳዩ | 606,000 | 202 ቡድን | 300 ብር/በወር | 10 ወራት |
| ከዋናው መ/ቤት የቁጥጥር ስራ | 175,000 | 25 ሰው | 70 ብር/በቀን | 100 ቀናት |
| የበረሃ አበል (የአበሉን 30 % እና የጠቅላላውን ጊዜ 10%) | 487,533 | | | |
| አበል (ለአካባቢ የአስተዳደር አካላት) | 0 | 0 | 0 | 0 |
| አበል (ንዑስ ድምር) | *16,738,633* | | | |
| 2. ስልጠና | | | | |
| ስልጠና በዋናው መ/ቤት | | | | |
| የጽሕፈት መሣሪያ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ትራንስፖርት- ለካርታ ሥራ አስተባባሪዎች መሄጃና መመለሻ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ትራንስፖርት- ለዋናው መ/ቤት ሰልጣኞች | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ትራንስፖርት- ለመስክ ሙከራ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| የምሣ አበል- ለዋናው መ/ቤት ሰልጣኞች | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ነዳጅ- ለአራት መኪኖች | 0 | 0 | 0 | 0 |
| የአዳራሽ ኪራይ- ለዋናው መ/ቤት ስልጠና | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ለአንድ ወር ለእረፍት ጊዜ ሻይ የሚወጣ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ሥልጠና- ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ሾፌሮች- የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችን የሚያመጡ | 0 | 0 | 0 | 0 |

# አማራጭ - 2 (1996)

የቆጠራ ካርታ ስራ የ1996 በጀት ፍላጎት 202 ቡድን

| የቆጠራ ዝግጅት | 1996 EFY | መጠን | ዋጋ | 1996 |
|---|---|---|---|---|
| ለመስክ ቁሳቁስ ጥገና (ድንኳን ፤ አልጋ ...ወዘተ.) | 50,000 | 202 ቡድን | 200 ብር/በቡድን | 10 ወራት |
| ጉልበት ሠራተኞች | 8,995 | 5 ሰው | 7 ብር/ቀን | 10 ወራት |
| የሌሎች (ንዑስ ድምር) | 10,078,375 | | | |
| ድምር (መጠባበቂያን ሳይጨምር) | 41,418,159 | | | |
| | | | | |
| መጠባበቂያ 20 ፐርሰንት | 0 | | | |
| | | | | |
| ጠቅላላ ድምር | *41,418,159* | | | |

# አባሪ ለአማራጭ - 2 (1996)

የመስክ ስራ በ 18 ወራት

ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት 202

| ተራ ቁጥር | ቁሳቁሶች | ጠቅላላ ብዛት | ያንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ |
|---|---|---|---|---|
| | በ1995 ዓ.ም መገዛት ያለባቸው አላቂ ቁሳቁሶች | | | |
| 1 | አዛሊድ ወረቀት (በጥቅል) | 300 | 300 | 90,000.00 |
| 2 | አሞኒያ ኬሚካል (ሊትር) | 1,000 | 1,000 | 1,000,000.00 |
| 3 | የስእል ቀለም (1.4) ሊትር | 130 | 162.00 | 21,060.00 |
| 4 | ላፒስ (የእርሳስና የቀለም) | 11,000 | 1.10 | 12,100.00 |
| 5 | እርሳስ (Sh.H.HB) | 36,000 | 0.50 | 18,000.00 |
| 6 | ማስኪንግ ቴፕ | 10,560 | 6.45 | 68,112.00 |
| 7 | ሙጫ | 2,718 | 4.80 | 13,046.40 |
| 8 | መቅረጫ (አነስተኛ) | 3,110 | 0.00 | 0.00 |
| 9 | ጠረጴዛ ላይ የሚታሰር መቅረጫ | 210 | 58.00 | 12,180.00 |
| 10 | እስክሪቢቶ (ጥቁር) | 7,770 | 1.03 | 8,003.10 |
| 11 | ማስታወሻ ደብተር ( 100 ገጽ) | 4,662 | 6.50 | 30,303.00 |
| 12 | ማርከር (መካከለኛ) ቀይ | 1,709 | 5.50 | 9,399.50 |
| 13 | ማርከር (መካከለኛ) የተለየ ቀለም | 1,709 | 5.50 | 9,399.50 |
| 14 | ሲሎ ቴፕ | 13,442 | 3.40 | 45,702.80 |
| 15 | ክላሰር | 73,000 | 0.80 | 58,400.00 |
| 16 | የስቴፕለር ሽቦ (ፓኬት) | 1,430 | 2.75 | 3,932.50 |
| 17 | መነሻ ካርታ 1:50000 | 13,224 | 0.00 | 0.00 |
| 18 | የፎቶ ኮፒ ወረቀት A3 (ፓኬት) | 540 | 129.00 | 69,660.00 |
| 19 | የፎቶ ኮፒ ወረቀት A4 (ፓኬት) | 202 | 43.40 | 8,766.80 |
| 20 | ሂቪ ዲዩቲ ባትሪ ድንጋይ በሳምንት 4 ለየቡድኑ ለ10 ወራት | 96,960 | 5.00 | 484,800.00 |
| 21 | የራዘር ምላጭ (ፓኬት) | 9,335 | 2.50 | 23,337.50 |
| 22 | ቾክ | 2,275 | 6.50 | 14,787.50 |
| 23 | ባትሪ | 222 | 12.00 | 2,664.00 |
| 24 | የባትሪ ድንጋይ | 13,332 | 4.00 | 53,328.00 |
| 25 | ተጣጣፊ ጠረጴዛ | 222 | 125.00 | 27,750.00 |
| 26 | ጃንጥላ | 1,144 | 0.00 | 0.00 |
| | ጠቅላላ ድምር | | | 2,084,732.60 |